PANORAMA # XXV

የትዝብት አድማስ

ግንቦት 15 2000

## ጀምሮ ማቋረጥና እስከ ድል ፍፃሜ መታገል የተለየ ከስተት ነው::

ከሠላሳ አምስት ዓመታት በፊት የጀመረውን ትግል ይዞ የቀጠለው ኃይል ተወደደም ተጠላ፣ ትግሉ ረዘመም አጠረ፣ መሥዋዕቱ ከበደም ቀለለ ዓላማው ከግቡ ሳያደርስ ትጥቁን እንደማይፈታ ከማንኛውም የኢትዮጵያ ጠላት በበለጠ ደህና አድርጎ የሚያውቀውና የሚረዳው ወያኔ እንደሆነ ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ነው:: የውጭ ደጋፊዎቹ ሁሉ ወያኔን ከተቃዋሚዎቹ ጋር ውይይት እንዲያደርግ በጠየቁት ጊዜ ሁሉ የሚሰጣቸው መልስ ከኢሕአፓ በስተቀር ከሌሎች ጋር ለመወያየት ዝግጁ መሆኑን እንደሚገልጽላቸው እነርሱም አይደብቁለትም:: ወያኔም ይህን መሳይ መልስ መስጠቱ አይፈረድበትም:: መራራው ትግልና የተከፈለውን መሥዋዕት በቀላሉ ረግጦ በተነሣበት ክቡር ዓላማ ላይ መደራደር የማይዋጥለት ኃይል ከወያኔ ጋር ለውይይት ቢቀርብ ምን ምን ነጥብ እንደሚያነሳ እራሱ ወያኔ አስቀድሞ ስለሚገባው፣ ይኽንን ኃይል የወያኔ መሪዎች ፊት ለፊት ለመቅረብ ድፍረቱም ሆነ አሳማኝ ነጥብ አይኖራቸውም:: ዱባና ቅል አበቃቀሉ እየቅል እንደሆነ ሁሉ ወያኔና ኢሕአፓ በአፈጣጠር፣ በይዘት፣ በዓላማና ግብ የጨለማና የብርሃን ያህል ልዩነት ስላላቸው፣ ወያኔ ኢሕአፓን የሚፈርጅው በአጥፊና ጠፊ ደረጃ በመሆኑ አያስገርምም:: ከወያኔ ጋር የመሬት፣ የርስትም ሆነ የድንበር ክርክር የለንም:: ከግለሰቦች ጋር ጠብም ይሁን ፍቅር አይኖርም:: ይህ ለወያኔ መሪዎች የሚተው ጉዳይ ነው:: እንደ ወያኔ በዘር ላይ ለተመሠረተ ፖሊሲ ኢሕአፓ ስለማይታገል ከወያኔ ጋር የዘርም ሆነ የግለሰብ ጥላቻና ችግር የለብንም:: በዚህም ላይ ሊቸግራቸውና ሊጨንቃቸው የሚችለው አሁንም የመለስ ዜናዊ ቡድንና ተከታዮቹ ብቻ ይሆናሉ:: እኛ ከወያኔ ጋር ያለን ችግር መሠረታዊ በሆነው በኢትዮጵያ ሕልውና፥ በሕዝቧ አንድነትና ልዕልና ላይ ነው:: ይህ እስካልተመለሰ ድረስ ትግሉን መጀመር/ መፈጸም የሚባል ነገር አይኖርም::

ጭብጥ አሻሮ ይዘህ ቁና ሙሉ ቆሎ ወደቋጠረ ተጠጋ በሚለው ስሌት በመመርኮዝ ለዘሌቄታው የኢትዮጵያ ጥቅም ሳይሆን ፣ ከጊዜያዊ ድግስ ለመቋደስ ተብሎ ትግሉን ማቋረጥም ሆነ በአጭር መቅጨት ሊሞከር ባለመታሰቡ ጥያቄው በመጀመርና በመፈጸም ሊታይ አይገባውም:: እኩል

የጀመረው ሁሉም እኩል ይፈጽማል ማለት አይደለም፡፡ መሠረታዊው ጥያቄ ሊሆን የሚችለው የትግሉ ዓላማና ግብ ዕልባት አግኝቷል? አላገኘም? ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ ጥያቄ ተገቢውን መልስ እስካለገኘ ድረስ ትግሉን መቀጠል አጠያያቂ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የትግሉን ፍጻሜ የሚወስነው የዓላማው መሳካት እንጅ የትግሉ መርዘም ወይም የሚጠይቀው መሥዋዕት ከባድነት አይደለም፡፡ በአስከፊ ሥርዓቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት የደቡብ አፍሪካ የነጮች አፓርታይድ ፖሊሲ ለመገርሰስ ከሰባ ዓመታት የበለጠ ዘመን መጠየቁም፣ የመጨረሻ ግቡ አፓርታይድን አስወግዶ የዜጎቹ መብት እኩልነት በሚያስከብር ሥርዓት ለመተካት ስለነበር፣ ዓላማው እስኪሳካ ትግሉ መቀጠል ነበረበት፡፡ የዛሬ ሠላሳ አምስት ዓመት ትግሉን የቀጠለው ትውልድም አሁንም በፅናት የሚታገለው ከዚህ መሠረታዊና ዓይነተኛ መርኅ በመነሳት ነው፡፡ በመሠረታዊ መርኅ ላይ ያልተገነባ ትግልም መልኅቅ እንደሌለው መርከብ ስለሚዋዥቅ የመሠረታዊ መርኅ ተገዥ መሆን ማለት የትግሉን መጀመሪያና መፈጸሚያ በሚገባ ተረድቶ ትግሉ ዒላማውን እስከመታ ድረስ በፅናት መታገል ማለት ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ ሃቅ ለወያኔዎቹ ይረቅቅባቸው እንደሁ እንጅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የትግል ሀ ሁ ነው፡፡ ያለፈው ጀግና ትውልድ÷ የሀገሩን ዳር ድንበር፣ ከውጭ ወራሪ ኃይሎች ጠብቆ ያቆየው÷ ሳይሰለች÷ሳይበገርና ሳይንበረከክ ያለማቋረጥ ሲታገል የነበር በመሆኑ ነው፡፡ የስድሣ ስድስቱ አብዮታዊ ትውልድም ይህን አኩሪ ጋሻ አንስቶ በፅናት ትግሉን በመቀጠሉ ሊያስደንቅ አይገባም፡፡ ሊያስስገርምና ሊያስደንቅም የሚችለው÷ የተነሳበትን ክቡር ዓላማና ሀገራዊ ቃል ኪዳን ዘንግቶ ተፍረክርኮ ቢቀር ነበር፡፡ ይህ ደግሞ የሚታሰብ አይደለም፡፡ በሌላው አኳያ ሲታይ ደግሞ÷በየጊዜው እንደየ ሁኔታው÷ እንደ እንጉዳይ በቅለው የሚጠፉት ድርጅቶችም የነበራቸውና ያላቸው ከባድ ችግር፣ የፖለቲካ ትግል ውጤት በአንድ ቀን ዝምበር የሚገኝ ስለሚመስላቸው ጭምር ነበር/ነውም፡፡ ትግል ከጡረታ በኋላ የሚመስላቸውና ሁኔታ እየተጠበቀ በወረት የሚካሄድ እየመሰላቸው ብቅ ጥልቅ እያሉ የሚብተከተኩ ክፍሎች ሁልጊዜ የማይገነዘቡት ዓቢይ ጉዳይ ቢኖር፣ ኢትዮጵያን ቀስፎ ከያዛት ጥልቅና መሠረታዊ ችግር ነፃ ለማውጣት ሙሉ ሕይወትና ታላቅ መሥዋዕት መጠየቁና ማስፈለጉ ነው፡፡ ትግሉን ከዳር ለማድረስ በግድ ሳይታክቱ፣ ሳይደክሙ፣ ማቄን ጨርቄ ሳይሉ ለማነኛውም ፈተናና ችግር ሳይበገሩ÷ በቀጣይነት መታገልን ይጠይቃል፡፡ የተጀመረው ትግል ዓላማው የተሳካ ሆኖ ግቡን እንዲመታ ካስፈለገ ቆራጥ የማይታክቱ ታጋዮች መኖር ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ ፈጣንና ተለዋዋጭ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንደ መስቀል ወፍ ብቅ ብሎ ለመክሰም ትግል እናካሂዳለን ብሎ መባከን ከአንድ ቀን ሰላማዊ ሰልፍ ዳንኪራና የስሜት ማስተንፈሻና እሮይታ አያልፍም፡፡ኢትዮጵያ ከዘረኝነት አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነፃ ለማውጣት፣ በግድ ኢትዮጵያዊ የአይበገሬነት ባሕርይና ቆራጥነት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ ለሁሉም ተሟልቶ እደማይሰጥ ያለፈው ሠላሳ ዓመታት የትግል ተመክሮ ሕያው ምሥክር ሆኗል፡፡ ደራሲ ከበደ ሚካኤል <u>አዝማሪና የውሃ ሙላት</u> በተሰኘው ግጥማቸው አንድ ስንኝ ውስጥ “ያልሰማው ሲመጣ የሰማው ሲሄድ” እንዳሉት በዚህ የሠላሳ አምስት

ዓመታት የትግል ሂደት ውስጥም አፍለኛው ሲመጣ የሰለቸው ሲሄድ መመልከት የተለመደ ክስተትና ትዝብት ሆኗል፡፡ ምንም እንኳ ትውልዱ ሁሉም በጠቅላላ ይህንን ሀቅ ይጋራዋል ባይባልም፣ ይህ ደግሞ የአያሌ ሺ ዓመታት የበለፀገ ታሪክ ባሕል ካለው ሕዝብ አብራክ የወጣ ትውልድ ባሕርይ ሊሆን ባልተገባው ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ የተጀመረው ትግል ዓላማውን እስካሳካ ድረስ አስፈላጊው መሰዋዕት እየተከፈለ እንደሚቀጥል እንኳንስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ጠላቶቹም ቢሆኑ ያለመጠራጠር ይቀበሉታል፡፡ ጀምሮ መተውና ፀንቶ መፈጸም የሰማይና የምድር ያህል ርቀት ስላላቸው፣ ጀምረው የተዉት ክፍሎች፥ ጸንተው ለመፈጸም የቀጠሉትን፥ ቢያንስ እንቅፋት ከመሆን ቢወስኑ ትግሉን እንደ ገፉት ይቆጠርላቸዋል፡፡ በትግል ሂደት፣ ከወገብሽ በታች ባለቤቴ ከወገብሽ በላይ እህቴ
የሚባል መሃል ሰፋሪነት ቦታ የለውም፡፡ ቀጥ ብሎ በዕምነት ፀንቶ መታገልና እስከ መጨረሻው የድል ምዕራፍ ድርስ በመዝለቅ፥ በታሪክም ሆነ በተተኪው ትውልድ ዘንድ አንፀባራቂ የታሪክ አምድ ሊያስመዘግብ ይችላል፡፡

ዛሬ የኢትዮጵያ ምዕራቡ ክፍል ከፅንፍ እስከ አፅናፍ ድርስ ወደ ሱዳን ሲሄድ፥ የሀገራችን ልዕዋላዊነት ሲደፈር፥ ዜጎቿ ታፍነው ተገድደው ሲሄዱ፥ እነኝህ ክፍሎች ድምፃቸውን አለማሰማቸው ብቻ ሳይሆን፥ ወያኔ ይህንን አይሰራውም በማለት ሀቁን ለመካድ ደፋ ቀና በማለት ላይ መሆናቸውን ስንታዘብ ብዙም ልንገረም አንችልም፡፡ ምክንያቱም ውሻ ለበላበት ስለሚጮኽ፥ከወያኔ የሚያገኙት ዳረንጎት እንዳይቋረጥባቸው የሚያድጉት የአድር ባይነት ባኅርያቸው ስለሆነ ነው፡፡ ተንበርካኪው ክፍል ሁሉ፥ በተፈጠረው በወቅቱ ሁኔታ አጋጣሚውን ለመጠቀምና በወያኔና በምዕራብ ኢትዮጵያ በሚመኖረው ሕዝብ መካከል በሚደረገው የሞት ሽረት ትግል፥ የማኅል ሰፋሪነት ሚና ለመጫዎት ካባቸውን በመቀያየር ላይ እንደሚገኙ ሕዝቡ ነቅቶባቸዋል፡፡ በሁለት ባላዎች ላይ በመንጠልጠልም ሁኔታውን በመዝረፍ ለወያኔ የእጅ መንሻ ለማቅርብ በመሯሯጥ ላይ ናቸው፡፡ እንዳንዶቹም፥ ይህ ጉዳይ የመላው ኢትዮጲያ ሕዝብ ጎዳይና ትግል መሆኑን በመካድ፥ “ ለምን የጎንደር ሕዝብ እራሱ መሬቱን አያስመልስም?” በማለት አሳፋሪና ከፋፋይ፥ አስተዛዛቢና ፀረ ኢትዮጵያ ንግግር በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ተደርሱባቸዋል፡፡ ምንም እንኳን ይህ
አሳፋሪ ድርጊታቸው፥ ለወያኔ መሪዎች እጅ መንሻ ለማቅረብ የሚጠቀሙበት የእበላ ባይነት መግባር ቢሆንም፥ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በየትኛው ክፍለ ሀገሩ ድንበር የሚጣሰው የግዛት ልዕልና የመላው የሀገሪቱ ድፍረትና ጥቃት መሆኑን ስለሚረዳ፥“ ክተት ሡራዊት ምታ ነጋሪት” ብሎ በአንድነት በመነሳት፥ እንደ አደዋውና እንደ ማይጨው፥ እንደ መቅደላውና መተማው፥ በጠላቱ ላይ ተባብሮ በመነሳት የሀገሩን ልዕዋላዊነት እንደ ሚያስከብር አንዳችም ብዥታ ሊኖር አይችልም፡፡

እነኝህ ክፍሎች፥ ትላንት ቅንጅትን በመከፋፈል የወያኔን አጀንዳ መፈፀማቸው አልበቃ ብሏቸው፥ ዛሬ ደግሞ አሁን የተፈጠረውን አጋጣሚ

በመጠቀም
የጎንደርን ክፍለ ሀገር ተወላጆች ለመከፋፈል፥ ሰላማዊ ሰልፍ ውጡ አትውጡ በማለት ለማወናበድና ሕዝባዊውን ትግል አቅጣጫ ለማሳት በመሯሯጥ ላይ እንደሚገኙ ተደርሶባቸዋል። ይህ እኩይ ተግባር የሚጠቅመው ወያኔን ብቻ መሆኑን ግን መታወቅ አለበት። ትላንት ከትላንት በስቲያ የጎንደርን ሕዝብ በማጋለጥና በማጋፈጥ ጥለውት የሸሹ መሆናቸውን ዘንግተው፥ ዛሬ እንደገና በሕዝብ ላይ ዳግማዊ ክህደት ለመፈፀም መከጀላቸው፥ ሕዝብን መናቅ ብቻ ሳይሆን፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ የማሰብ ችሎታና የአዕምሮ ልዕልና እንደመሳደብም ይቆጠራል። ይህ ደግሞ ውሎ አድሮ የሚያስከትለውን ሰበብና ታሪካዊ ጠንቅ መረዳት በተገባ ነበር። ይህን በጊዜያዊ የፖለቲካ ብልጠት ላይ የተመሰረተ ደባ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ እንዲያስትውልው ይገባል። ትግሉን በፅናት የቀጠለው ክፍል፥ ከኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ ብሔራዊ ጥቅም አኳያ በማየት ይታገላል እንጅ፥ ለጊዜያዊ የፖለቲካ ዘማዊነት ደረጃውን ዝቅ አድርጎ ሕዝብን በመከፈፈል ሂደት ውስጥ እራሱን አያስማራም።